1084
857

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር
Ref.No ግ/ሒ/2/70
ቀን
Date 06/04/2009

ለፌዴሬሽን ምክር ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

የፌዴራል መንግሥት ግዢ ስለሚፈፀምበት አኳኋን በገንዘብ መጠን ተወስነው የተቀመጡት ገደቦች ከወቅቱ የገንዘብ የመግዛት አቅም ጋር እንዲጣጣሙ እንዲሁም በግዢ አፈፃፀም አድልዎ እንዳኖር በር የሚከፍቱ አንቀፆች እንዲስተካከሉ ለማድረግ በፌዴራል የመንግሥት የግዢ አፈፃፀም መመሪያ ላይ ታህሳስ 1 ቀን 2008 ዓ.ም. በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተፃፈ ደብዳቤ በወጣው መመሪያ ማሻሻያ መደረጉ ይታወሳል፡፡

ሆኖም ማሻሻያ መመሪያው ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ አንዳንድ የመመሪያው አንቀጾች የአፈፃፀም ችግር ማስከተላቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዚህም መሠረት የአፈፃፀም ችግር አስከትለዋል የተባሉት አንቀፆች ተመርምረው ማሻሻያ ተደርጐባቸዋል፡፡

ስለዚህ የማሻሻያ መመሪያውን 2 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ ከታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብርሃም ተከስተ (ዶ/ር)
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

Letter/HB./TA

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ.
P.O.Box1905,1037
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia
እባክዎን መልስ ሲፅፉ ለን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ

# የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈጻጸም መመሪያን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ መመሪያው ከዚህ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ማሻሻያ

የፌዴራል መንግሥት የግዥ አፈፃፀም መመሪያን ለማሻሻል የወጣው መመሪያ እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል።

1. የመመሪያው አባሪ ፩ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሀ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሀ" ተተክቷል።

   "3(ሀ). የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮች ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ሊሠራ ከታሰበው የግንባታ ሥራ ጋር ተመሳሳይ በሆነ ቢያንስ አንድ የግንባታ ሥራ በሥራ ተቋራጭነት፣ በሽርክና ማኀበር አባልነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት የሠሩና ከሚወዳደሩበት ሥራ በዋጋ ቢያንስ 70% (ሰባ በመቶ) የሆነን ሥራ በአስተማማኝና በአጥጋቢ ሁኔታ ማጠናቀቅ አለባቸው።"

2. የመመሪያው አባሪ ፩ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሐ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 3 ፊደል ተራ "ሐ" ተተክቷል።

   "3(ሐ). የግንባታ ሥራው ግምት ከብር አንድ ቢሊዮን እና ከዚያ በላይ ሲሆንና፣ ሥራ ተቋራጮች በፊደል ተራ "ሀ" ላይ የተጠየቀውን የተዛማጅ ሥራ ልምድ ዋጋ በአንድ ፕሮጀክት በሠሩት የሥራ ልምድ ብቻ ማሟላት ካልቻሉ በአጥጋቢ እና በአስተማማኝ ሁኔታ የተጠናቀቁ ሁለት ወይም ሶስት ፕሮጀክቶች ድምር በልምድነት ሊያዝላቸው ይችላል። ሆኖም የሁለቱ ወይም የሶስቱ ፕሮጀክቶች የተናጠል ዋጋ ማሟላት ከሚገባቸው የሥራ ልምድ ዋጋ እንደቅደም ተከተላቸው ከግማሽ (1/2) ወይም ከሲሶ (1/3) በታች መሆን የለበትም።"

3. የመመሪያው አባሪ ፩ ተራ ቁጥር 5 ፊደል ተራ "ሀ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 5 ፊደል ተራ "ሀ" ተተክቷል።

"5(ሀ) የሀገር ውስጥ ሥራ ተቋራጮችን በተመለከተ ለጨረታ ግምገማ ዓላማ የሚወሰደው በግንባታ ላይ ካለና ከተጠናቀቀ የግንባታ ሥራ ላይ የተሰበሰበ ክፍያ ዓመታዊ ተርንኦቨር ተቋራጩ ባለፉት አምስት ዓመታት ካስመዘገበው የግንባታ ሥራ ዓመታዊ ተርንኦቨር መካከል የተሻለውን በመምረጥ ሆኖ፣ ሥራ ተቋራጮች እንዲያሟሉ የሚጠየቁት የተርንኦቨር መጠን የሚሰላው ሊሠራ የታሰበውን የግንባታ ሥራ ግምታዊ ዋጋ፣ ቀናትን ወደሚቀጥለው ሙሉ ወር በማጠጋጋት ግንባታው ይጠናቀቃል ተብሎ በሚገመትበት ወርሃዊ ጊዜ በማካፈል እና ውጤቱን በ12 እና በ0.8 በማባዛት ይሆናል። ለምሳሌ፣ አንድ ፕሮጀክት በሁለት ዓመት ከአንድ ወር ከ10 ቀን የሚጠናቀቅ ቢሆንና የዋጋ ግምቱ ብር 100 (አንድ መቶ) ሚሊዮን ቢሆን ሂሳቡ እንደሚከተለው ይሰላል።"

$$\frac{100{,}000{,}000}{26} \times 12 \times 0.8 = \text{ብር } 36{,}923{,}077$$

4. የመመሪያው አባሪ ፲ ተራ ቁጥር 12 ፊደል ተራ "ሀ" ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር 12 ፊደል ተራ "ሀ" ተተክቷል።

"12(ሀ). ለመንገድ ፕሮጀክቶች የግንባታ ሥራ የሚወዳደረው የአገር ውስጥ ሥራ ተቋራጭ ሲሆን፣ ሊሠራ ከታሰበው የመንገድ ሥራ በአንድ ደረጃ ዝቅ ያለ ልምድ ተቀባይነት ይኖረዋል። ነገር ግን የመንገድ ግንባታ ስራው የዋጋ ግምት ከብር 400 (አራት መቶ) ሚሊዮን በታች በሚሆንበት ጊዜ ሁለት ደረጃ ዝቅ ያለ እና ከዚያ በላይ የሆነ ፕሮጀክት ለተዛማጅ ስራ ልምድነት ሊያዝ ይችላል።"

## 3 ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም

ዶ/ር አብራሃም ተከስተ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር

Der/Hb/TA